# COMMONWEALTH of VIRGINIA
## Virginia Employment Commission

Commission Appeals, P.O. Box 26441, Richmond, Virginia 23261-6441
804-786-4140 · FAX 804-786-9034


## **የይግባኝ ማስታወቂያ**

A-CLA-010

SSN:
መዝገብ:

**<u>አቤቱታ አቅራቢ</u>**

**<u>ተጠያቂ አሰሪ</u>**

**<u>ቀጣይ አሰሪ</u>**

የአቤቱታ አቀረታቢውን የስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች ክፍያ ጥያቄ አስመልክቶ በ<FLA ውሳኔው በመልዕክት የተላከበት ቀን> ከተላከው የይግባኝ መርማሪ ውሳኔ በመነሳት ይግባኝ ተመዝግቧል/ቀርቧል። ይግባኙ ቀን <የመዝገብ ቀን> የተጻፈበት ሲሆን አስመዝጋቢው <የይግባኝ ባይ አይነት> ነው።

### **የኮሚሽን ይግባኞች**
(ከይግባኝ መርማሪ ውሳኔ በመነሳት የሚቀርቡ ይግባኞች)

ሁሉም ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ ይግባኞች በይግባኝ መርማሪው በሚዘጋጀው መዝገብ ሰር በሚካተተው ማስረጃ ላይ በሚካሄድ ምርመራ መነሻነት ውሳኔ ያገኛሉ። ኮሚሽኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ወዲያውኑ ችሎት መስሚያ ቀጠሮ አይይዝም። አንደኛው ወገን ተጨማሪ ምስክርነት የሚያሰማበት፣ ማስረጃ የሚያቀርብበት ወይም የቃል ክርክር የሚያደርግበት ችሎት እንዲሰማለት የሚፈልግ ከሆነ ምክንያቶቹን የሚገልጽ የጽሁፍ ጥያቄ ይህ ማስታወቂያ በመልዕክት ከሚላክበት ቀን ጀምሮ በአስራ አራት (14) ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ የችሎት መዝጋቢ መቅረብ አለበት። በአጠቃላይ ሁሉም የኮሚሽኑ ችሎት መስማቶች በሪችሞንድ፣ ቨርጂኒያ በአካል ይካሄዳሉ። ሆኖም ኮሚሽኑ ሁሉም ወገኖች የሚስማሙ ከሆነ የቃል ክርክር የሚካሄድባቸው ችሎቶች በስልክ ኮንፍረን እንዲካሄዱ ሊፈቅድ ይችላል።

የኮሚሽኑ ልዩ መርማሪዎች ኮሚሽኑ ተጨማሪ ማስረጃ መውሰድ ያለበት ስለመሆን አለመሆኑ ለማዘዝ በሚወስኑበት ወቅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች መከተል አለባቸው። ኮሚሽኑ በራሱ በራሱ ብይን በአንደኛው ወገን በሚቀርብለት ማመልከቻ በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲወሰድ ሊያዝ ይችላል:

1. በአዎንታዊ መልኩ ተጨማሪ ማስረጃው (ሀ) አግባብነት ያለው እንጂ ጥቅል ብቻ አለመሆኑ፣ ለራሱ ለብቻው የሚያስረዳው ወይም ዋስትና የሚያደርገው ነገር አለመኖሩ ሲታወቅ እና (ለ) በቀዳሚው ችሎት ላይ ተገቢ ጥንቃቄን በማድረግ ምክንያት ሊቀርብ አለመቻሉ ሲታወቅ እና (ሐ) ለአዲሱ ችሎት የተለየ ውጤት ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ሲታመን፤ ወይም
2. ቀደም ሲል በይግባኝ መርማሪ ፊት የተካሄዱ ክርክሮች መዝገብ ኮሚሽኑን ተገቢ፣ ትክክለኛ ወይም የተሟሉ የዝርዝር ግኝቶች ወይም የህግ ድምዳሜዎች እንዲያገኝ ለማስቻል በቂ አለመሆኑ ከታወቀ።

ይህ የይግባኝ ማስታወቂያ በ<የመልእክት ቀን> ተልኳል።

የኮሚሽኑ ችሎት ፀሀፊ

**እያንዳንዱን ወገን የተመለከተውን ጠቃሚ መረጃ ከጀርባ ጎኑ ላይ ያንብቡ።**

**ለእያንዳንዱ ወገን የተሰጠ ጠቃሚ መረጃ**
(አቤቱታ አቅራቢዎች እና አሰሪዎች)

**ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎች:** አቤቱታ አቅራቢው እነዚህን ጥቅማ ጥቅሞች የማግኘት ብቁነት ከሳምንት ሳምንት መነሻነት ላይ እንደሚመሰረት ማወቅ አለበት። ይግባኙ በይደር ተይዞ በሚቆይበት ወቅት ቀጣይነት ያለው የጥቅማ ጥቅሞች መብትዎን ለማስከበር እንዲቻል ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎችዎን ማስመዝገብዎን መቀጠልዎ አስፈላጊ ነው። የይገባኛል ጥያቄዎችዎን በአግባቡ አለማስመዝገብ ጥቅማ ጥቅሞችዎን እንዲከለከሉ ሊያደርግ ይችላል። አቤቱታ አቅራቢው ሙሉ በሙሉ በተቀየረ ውሳኔ ምክንያት ክፍያዎችን የሚያገኝ ከሆነ የጥቅማ ጥቅሞች መልሶ ክፍያ መክፈል ያስፈልጋል።

**የአድራሻ ለውጥና መውጣት:** ይግባኙ በይደር በተያዘበት ሁኔታ አድራሻዎን የሚቀይሩ ከሆነ፣ ወይም ይግባኝ ባዩ ወገን ከይግባኙ ለመውጣት የሚፈልግ ከሆነ ይህን በአስቸኳይ በፊት ገጽ የላይኛው ጫፍ ላይ በተመለከተው አድራሻ ለኮሚሽኑ የችሎት መዝጋቢ ማሳወቅ ያስፈልጋል። የአድራሻ ለውጥን በዩኤስ የፖስታ አገልግሎት በኩል ማስመዝገብ ብቻ በኮሚሽኑ የተያዘውን አድራሻዎን ለመቀየር በቂ አይደለም።

**ጠበቃ መቅጠር:** ጠበቃ መቅጠርዎ አስፈላጊ ነው ብለው ካሰቡ የዚህን አገልግሎት ክፍያ መክፈል አለብዎት። በማህበረሰብዎ ውስጥ ካለው የህግ እርዳታ/ድጋፍ ማህበር ጋር በስልክ ቁጥር 1-866-534-5243 በመነጋገር ነጻ የህግ አገልግሎቶችን ሊያገኙ ይችላሉ። በተጨማሪም የቨርጂኒያ ግዛት መስመርን የህግ ባለሙያ ሪፈራል አገልግሎት በስልክ ቁጥር 1-800-552-7977 ደውለው በማነጋገር ጠበቃ ሊያገኙ ይችላሉ። ጠበቃ የሚቀጥሩ ከሆነ የጠበቃዎን ስም፣ አድራሻና ስልክ ቁጥር በቨርጂኒያ የስራ ቁጥር ኮሚሽን፣ የመ.ሣ. ቁጥር 26441፣ ሪችሞንድ፣ ቨርጂኒያ 23261 ለሚገኘው የኮሚሽኑ የችሎት መዝጋቢ መስጠት አለብዎት።

ይህ የይግባኝ ማስታወቂያ በ <ቀን> ለሚከተለው አካል በመልዕክት ተልኳል: